# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

17




ታኅሣሥ ፴—፲፱፻፸፱ ዓ. ም.

## ርእሰ አንቀጽ

# ዓለም አቀፍ ሴራ

እንደማንኛውም አብዮት የኢትዮጵያም አብዮት ወዳጆችና ጠላቶች በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም ይገኛሉ ። እንደማንኛውም አብዮት የኢትዮጵያም አብዮት እየገፋና ጠላቶቹን እያፐለቀለቀ በሔደ ቊጥር እነዚህ የውስጥና የውጭ ጠላቶች መግጠማቸው የማይቀረው የአድኀሪ ኃይሎች ሥርዓተ መቃብር ወግ ነው ። በአገር ውስጥ የአንድ አብዮት መግፋት ልዩ ልዩ መደቦችን እያንሸራተተ ወደፀረ አብዮቱ ሠፈር የሚደባልቃቸውን ያህል ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም እንደዚሁ የመደቦች መንሸራተት ፤ የኃይሎች አሰላለፍ መቀያየር በአንድ አብዮት ሒደት ላይ የማይቀር ነገር ነው ።

በኢትዮጵያ አብዮት ሒደት ብዙ መደቦችና የኅብረተሰብ ክፍሎች አብዮቱ እየገፋ ሲሔድ እንደከዱትና ከጀርባው ሊወጉት እንደሞከሩ ለመረዳት ከየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ወዲህ ጠብ ጠብ እያሉ የቀሩትን ኃይሎች መመልከት ብቻ ይበቃል ። በዓለም አቀፍ ደረጃም ይህ ዓይነቱ የኃይል አሰላለፍ ለውጥ አለ ። ትላንት ከፋሽስቱ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጋር ባላቸው የመደብ ጥቅም መግጠም የተነሣ ፊውዳል ኢትዮጵያን እንደወዳጅ ይቆጥሩ የነበሩ መንግሥታት ፤ ዛሬ የኃይለ ሥላሴን ፋሽስታዊ አገዛዝ አሽቀንጥራ ጥላ አዲስ ኑሮ ለመገንባት በመጣጣር ላይ ያለችውን አብዮታዊት ኢትዮጵያን በክፉ ዓይን ከመመልከትም አልፈው ሊያጠፏት ይሞክራሉ ። በዚሁ አንፃር ደግሞ በፋሽስቱ በአፄ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ ሥር ፊውዳል ኢትዮጵያን ለነፃነት ትግላቸው ዕንቅፋት አድርገው ይቆጥሯት የነበሩ የአካባቢው ጭቁን ሕዝቦችና ተራማጅ መንግሥታት አብዮታዊት ኢትዮጵያን ዛሬ እንደጠንካራ አጋር ፤ እንደጠንካራ ወዳጅ ይቆጥሯታል ።

ከመደብ ጥቅማቸውና ትግላቸው አንፃር ስናየው ፤ ሁለቱም እውነት አላቸው ። ፀረ አብዮት ኃይሎችን እንውሰድ ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ፀረ ኢምፔሪያሊስት እንደመሆኑና የዓለም ሶሻሊስት አብዮት የማይነጠል አጋር እንደመሆኑ መጠን የትግሉ መሳካትና በዚች በአፍሪካ አህጉርና በዓረብ ዓለም ወሰን ላይ በምትገኝ ምድር ጠንካራ ፤ አብዮታዊትና የበለጸገች አገር መገንባት ለኢምፔሪያሊዝምና ለአካባቢው አድኀሪ ኃይሎች እጅግ አደገኛ ሁኔታን ይፈጥራል ። ለውስጥ አድኀሪዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ «ጨዋነትና አስተዋይነት» የነሱን ብዝበዛና ጭቆና አሜን ብሎ እስከ ተቀበለ ብቻ የነበረውን ያህል ፤ የዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና ለጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል አልፏቸው ለሔዱ የአካባቢው መንግሥታትም «የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋይነት ፤ የኢትዮጵያ ወዳጅነት» ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀንደኛ ጠላቶቹን እየገረሰሰ ዕድሉን እጁ ማስገባት የጀመረለት አክትሟል ። አብዮታዊት ኢትዮጵያ ወዳጅ ልትሆናቸው አትችልም ። ስለሆነም በአገር ውስጥ ከሚገኙ ፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር በመተባበር አብዮታዊት ኢትዮጵያን ማዳከምና መደምሰስ ፤ የውስጥና የውጭ አድኀሪዎች የመደብ ጥቅም የሚጠይቀው ጉዳይ ነው ።

በዚሁ አንፃር ደግሞ ፤ የዓለም ተራማጅ ኃይሎችና በተለይም የአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች አብዮታዊት ኢትዮጵያን በተስፋና በወዳጅነት ዓይን ቢመለከቷት ይገባናል ። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ሥር የነበረችው ፊውዳል ኢትዮጵያ የአካባቢውን ሕዝብ የነፃነት ተጋድሎ ለማፈን ኢምፔሪያሊስቶች የሚገለገሉባት ፤ ለነሱና ለአካባቢው አድኀሪ መንግሥታት በታማኝነት የቆመ ፋሽስታዊ አገዛዝ የሰፈነባት አገር ነበረች ። በዚሁ ልክ ለአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች ትግል ፀር ነበረች ። ዛሬ ግን በዚህ አካባቢ አብዮታዊት ጠንካራና የበለጸገች ኢትዮጵያ መመሥረቷ በጠቅላላው የአካባቢውን አድኀሪዎች ከማዳከምም አልፎ ሌላው ቢቀር የኢትዮጵያ ጭቁኖች በአካባቢው በሚያንጸባርቁት የትግል ምሳሌነት እንኳን ለአካባቢው ጭቁኖች ብርታትና ሞራል የሚሰጥ ሁኔታ መሆኑን ያውቁታል ። በዚህ የተነሣ እንደዲሞክራሲያዊት የመን የመሳሰሉ አብዮታዊ መንግሥታትና የአፍሪካና የአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች ለኢትዮጵያ አብዮት መሳካት መጨነቅና መጠበብ ቢያሳዩ ይገባናል ።

ዓለም አቀፍ አድኀሪ ኃይሎች አብዮታዊት ኢትዮጵያን በክፉ ዓይን በመመልከት አይቆጠቡም ። ትላንት ከፊውዳል ኢትዮጵያ ጋር የነበራቸው ወዳጅነት ከፋሽስቱ ኃይለ ሥላሴ ጋር እጅና ጓንቴ ሆነው በጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሰፍኖ ለነበረው አረመኔ አገዛዝ ተባባሪ አድርጓቸው ነበር ። ዛሬ ደግሞ ለአብዮታዊት ኢትዮጵያ ያላቸው ጠላትነት ከመሣፍንት ፤ ከመኳንንት ፤ ከኢ.ሕ.አ.ፓ. ፤ ከኤርትራ አድኀሪ ግንባሮች ፤ ከሲ.አይ.ኤና በጠቅላላው ከቀልባሽ ኃይሎች ጋር በአንድነት ሆነው የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ እንዲያሤሩ ያደርጋቸዋል ።

ከየካቲት ፷፮ ወዲህ በኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች የአብዮታዊ ትግል አጭር ታሪክ ውስጥ ከዚህ የተለየ ነገር አላየንም ። የኢትዮጵያ አብዮት ወደፊት እየገፋ በሔደ ቁጥር ኢምፔሪያሊስቶች ፤ ፊውዳሊስቶችና የአካባቢው አድኀሪ መንግሥታት ለአብዮታችን ያላቸው ጥላቻ ፤ እሱንም ለማጥፋት የሚያደርጉት መፍጨርጨር እየጨመረ የትግል ትብብራቸውም የዚያኑ ያህል እየዳበረ በመሔድ ላይ ነው ። ዛሬ በአካባቢያችን ያሉት አድኀሪ መንግሥታት ከሳውዲ ዓረቢያ መሣፍንት አንሥቶ እስከ ፀረ ኮሙኒስቱ ንዑስ ከበርቴ እስከ ኒሜሪ ድረስ ያሉት ፀረ ሕዝብ መንግሥታት በዚህ አካባቢ አብዮታዊትና ጠንካራ የሆነች ኢትዮጵያ እንድትኖር አይፈልጉም ። ስለሆነም በአገር ውስጥ ካሉት ፀረ አብዮት ኃይሎች ጋር በመተባበር አብዮቱን ለመቀልበስ በመሯሯጥ ላይ ይገኛሉ ።

ይህ የቅልበሳ ሤራ የተጀመረው ዛሬ አይደለም ። እንዲያውም አብዮታችን እዚህ የደረሰው የውስጥ አድኀሪዎችን ኃይልና ቅስም ብቻ እየሰበረ ሳይሆን ፤ ዓለም አቀፍ አድኀሪዎችና የአካባቢው አድኀሪ መንግሥታት በፕሮፓጋንዳ ደረጃ የሚያደርጉትን የማጥላላት ዘመቻ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ በገንዘብና በስንቅ እየደራጁ የሚልኩበትን ሠርጎ ገቦችና ፀረ አብዮት ኃይሎችም እየተቋቋመ መሆኑ ግልጽ ነው ። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ለኢትዮጵያ አንድነት ተቆርቋሪ ይመስሉ የነበሩ ኢምፔሪያሊስቶችና እነኒሜሪ ዛሬ ለኤርትራ ግንባሮች የመገንጠል ዓላማ በይፋ ቢተባበሩ ፤ በዚህ ሁኔታ በሚፈጠረው ውጥረት የኢትዮጵያን አብዮት ለቀልባሾች እናመቻቻለን በሚል ቅዠት እንጂ ፤ ለጭቁኖች ነፃነት ተቆርቋሪዎች ሆነው እንዳይደለ ኢምፔሪያሊስቶችና አድኀሪዎች በያለበት ጨቁነው የያዟቸው ሕዝቦች ምስክር ናቸው ።

በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ተራማጅ የኢትዮጵያ ስደተኞችን እያፈኑ ለፋሽስቱ መንግሥት ሲያስረክቡ የነበሩ አድኀሪዎች ዛሬ የኮበለሉ መሣፍንትንና በአብዮቱ የተተፉ ንዑስ ከበርቴዎች ቀጥር ነፍሰ ገዳዮችን በግዛታቸው ውስጥ በይፋ እያሠለጠኑ ለፀረ አብዮት ተግባር ወደኢትዮጵያ ሠርገው እንዲገቡ ማድረጋቸው ምንጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያን ጭቁን ሕዝቦች አብዮት የሚፈሩ ፀረ ሕዝቦች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ተግባር ነው ።

ኒሜሪ የፊውዶ ፋሽስቱ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ጥሏቸው የሔደውን ችግሮች ለመወጣትና ከፀረ አብዮት ኃይሎች እየተከላከለች አዲስ ኑሮ ለመገንባት በመተናነቅ ላይ ያለችውን አገራችንን

«ልትወረኝ እየተሰናዳች ነው» ብሎ ቢለፍፍና ለዚህም በሬ ወለደ ፕሮፓጋንዳው እነ ኢ.ዲ.ዩ «ኢትዮጵያ የጐረቤት አገሮችን ሰላም ለማደፍረስ ትሞክራለች» ቢሉ፣ እነ ኢ.ሕ.አ.ፓ ደግሞ «እንደፋሽስቱ ሂትለር ኢትዮጵያም ጐረቤት አገሮችን ለመውረር እየተጋበዘች ነው» እያሉ ቢያስተጋቡለት፣ እነዚህ የውስጥና የውጭ አድኃሪዎች በአብዮታዊት ኢትዮጵያ ላይ ለሚያደርጉት ወረራ የተቀነባበረ የፕሮፓጋንዳ ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆናቸውን በይፋ ይታይባቸዋል እንጂ፣ የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ አብዮቱን ፈር ለማስያዝ በየአቅጣጫው እጅግ መራራ የሆነ ትግል በሚያካሂድበት በዛሬው ወቅት፣ ጐረቤት አገሮችን ሊወር ነው የሚለውን በሬ ወለደ የሚያምንላቸው ማንንም አያገኙም።

በዚህም «ልወረር ነው» በሚል ሳቢያ የሱዳኑ ፕሬዚዴንት ኒሜሪ «ከፈለግሁኝ ወደኢትዮጵያ ፭፻ሺህ ኢትዮጵያውያንን አስታጥቄ ለመላክ እችላለሁ» በማለት መደንፋቱን የዓለም ዜና ወኪሎች እያስተጋቡ ጽፈዋል። እንዲህ ዓይነቱ አነጋገር ራሱ የኢትዮጵያን አብዮት ለመቀልበስ የሚጠነሰሰው ዓለም አቀፍ ሤራ ከፕሮፓጋንዳና ከሠርጎ ገብነት ደረጃ ተሸጋግሮ ወደቀጥታ ጣልቃ ገብነት ደረጃ ለመተላለፍ መዘጋጀት የሚያሳይ ልፈፋ ነው። ነገር ግን እነኒሜሪ የመሣፍንቱን፣ የኢ.ሕ.አ.ፓንና የአድኃሪዎቹን የኤርትራ ግንባሮች ቅጥረኞች እያስታጠቁ በመላክ ብቻ በአገራችን ምድር ከዳር እስከ ዳር ሥር የሰደደውን አብዮት እንቀለብሳለን ብለው ገምተው እንደሆን እጅግ ተሳስተዋል። እነሱ አብዮታችንን ለመቀልበስ ቢበዛ በሺህ በሚቆጠሩ ቅጥር ነፍስ ገዳዮች ይተማመኑ ይሆናል። ነገር ግን ዓለም አቀፍ ፀረ አብዮት ኃይሎች እያስታጠቁ ወደምድራችን በሚልኩት አንድ ፀረ ሕዝብ ነፍስ ገዳይ፣ የኢትዮጵያ አብዮት በሺህ የሚቆጠሩ አብዮታውያንን ሊያሰልፍበት እንደሚችል መገንዘብ ይኖርባቸዋል።

ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአካባቢው በሚገኙ የነገሥታት፣ የከበርቴዎች እና የቀኝ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ አድኃሪ መንግሥታት በኩል የሚደረግበትን ግፊትና ጥቃት፣ የመቋቋሙን ተግባር አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ ከሚያደርገው መራራና የተወሳሰበ ትግል ነጥሎ አይመለከተውም። ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ዛሬ የገዛ ዕድሉ ባለቤት ለሆነባት አብዮታዊት እናት አገሩ ይቅርና ትላንት ለጥቂቶች ቅንጦት እሱ ፍዳውን ሲቆጥር ለነበረባት አገሩ ደሙን ሲያፈስ አጥንቱን ሲከሰክስ የታወቀና የተደነቀ ሕዝብ ነው። ስለሆነም ከውስጥና ከውጭ አድኃሪ ኃይሎች ሤራቸውን አቀነባብረው ከየአቅጣጫው ሊያዋክቡት ቢሞክሩም፣ ዓለም ያደነቀውን የአገር ፍቅር ስሜቱን ከአብዮታዊ ንቃት ጋር አዋህዶ ለነፃነቱ፣ ለክብሩና ለብልጽግናው የጀመረውን ታሪካዊ ተጋድሎ ከግቡ እንደሚያደርሰው፣ ለዚህም አስፈላጊ የሆነውን መሥዋዕትነት ለመቀበል ዝግጁ መሆኑን ማንም ሊያውቀው ይገባል።

ዛሬ ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰበት ከፍተኛ የአብዮታዊ ንቃት ደረጃም በዚህ ትግሉ ብቻውን እንዳይደለ ጠንቅቆ ያውቃል። የዓለም ጭቁን ሕዝቦችና ተራማጅ ኃይሎች በተለይ ደግሞ የጐረቤትና የአካባቢው አገሮች ጭቁን ሕዝቦችና ተራማጆች በበኩላቸው ከተጫኑባቸው አድኃሪ መንግሥታትና ከአጋሮቻቸው ከኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚታገሉ መሆናቸውን ይረዳዋል። የእነሱንም ትግል የሱ ትግል፣ ድላቸው ምንም የራሱ ድል አድርጎ ስለሚመለከተውና ጭቁን ሕዝቦች በያሉበት ከጐኑ እንደተሠለፉ ስለሚያውቅ በበለጠ ቆራጥነት ይህን ዓለም አቀፍ ሤራ ተቋቁሞና ደምስሶ ፍትሕና ሰላም የሰፈነባት ዓለም ለመገንባት ለሚደረገው ታሪካዊ ትግል ድርሻውን ያበረክታል።